# በባሌ ወይንስ በቦሌ ክርክር እና ያስቆጠረው የአርባአመት እድሜ !!!

መንግስቱ

**Dec 10 at 7:48 PM**

ወያኔ አዲስ አበባን ከመያዙ አመት ወይንም ሁለት አመት ቀደም ብሎ ኢዴሐቅ የተባለ ስብስብ ተፈጥሮ ነበር። ይህን ስብስብ የፈጠሩ ሀይሎች በእውነት መጭው ጊዜ ታይቷቸው ቢሆንም በውስጡ ያካተቷቸው ግለሰቦች እና አንድንድ ድርጅት ነን ባይ የግለሰብ ስብስቦች ምንም እራእይም ሆነ በራሳቸው አስበው የሚሰሩት ያልነበራቸው በመሆኑ በስደት በሚኖሩበት ኑሮአቸውን የሚሞሉላቸው የውጭ ሀይሎች ታዛዥ እና ነገር አቀባባይ ስለነበሩ ስብስቡን ፋይዳ ያለው ቁምነገር እንዳይሰራ ተብትበውት እንደነበር በቁጭት ይታወሳል። መቸም አቶ ክፍሌ ወዳጆን ማስታወሱ ወይንም አቶ ደረጀ ደሬሳን ስራወች መዘከሩ በቂ ይሆናልና ነው።

አፈሩ ይቅለላቸው እና እነዚህ መሰል ግለሰቦች በውስጡ ያካተተው ኢዴሐቅ ውሎ አድሮ የውጭ ሐይሎች ታርጌት መሆኑ አልቀረና ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በክፉ ቀን የሚጮህላት ሳይኖር ልጆቿ በዚህ ስብስብ አማካኝነት ደርጉን የአገር አድን ጥሪ ከመጥራት ጀምሮ እስከ ሎንዶን የጠላት ኮንፍረንስ ቢሟገቱም ከውስጣቸው የተሸከሟቸው ግለሰቦች ለሌሎች ሀይሎች ቅጥረኛ የሆኑት ወያኔ አዲስ አበባን ስትቆጣጠር በትእዛዝ መግባታቸውን የቅርብ ትውስታችን ነበር።

ከዚያ ቀደም ባለው የየካቲት አብዮት እንዲሁ የህሊናዊ ሁኔታወች ሞልተው በተረፉበት ወቅት የግዜው ቀርቧል አልቀረበም ክርክር የት እንዳደረሰንም የምንዘነጋው አይደለም። በመኢሶን እና በኢሕአፓ የነበረው ልዩነት ደርጉ ጠላት ነው አይደለም እሰጥ አገባ መዝጊአው ምን እንደነበርም ዛሬ በቁጭት የምንዘክረው ተውኔት ነበር። እዚህ ላይ ማን ተሳሳተ ማንስ ትክክል እርምጃ ወሰደ ሳይሆን በመሰረታዊ ጠላትና በመሰረታዊ ወዳጆች መካከል ያለው ልዩነትና ትሥር ባገራችን ፖለቲካ ላለፉት 40 አመታት የማይገባ ደም አፍሷል። ትግሉን ስቦ ከገደል ጨምሮታል።

የዴሞክራሲ፤ የመብት እና የመሰረታዊ የህዝብ ልእልናን የማስከበር ጥያቄወችን ወደጎን አስቀምጦ የእሰጥ አገባ ፍትጊአው ጠላትን ከደደቢት እስከ ሚኒሊክ ቤተመንግስት እስኪገባ ኸናግቶናል። ነገርን ነገር ያነሳዋልና በዚያን በየካቲት አብዮት መባቻ ዶክተር ሰናይ ልኬ የተባሉ የሰሜን አሜሪካ የተማሪው ማህበር አባል በኋላ ወዝሊግ የተባለውን ስብስብ መስራች ነፍሳቸውን ይማርና በቦሌ ሳይሆን በባሌ ለመግባት ብዙ ዝግጅት ከፈጸሙ በኋላ ያሉት ሳይሆን ተቃራኒውን ተከትለው እንዴውም ከደርጉም አብረው እና የነጻው እርምጃም ፊታውራሪ ሆነው እንዴት ህይወታቸው እንዳለፈች የዚያ ክፉ ዘመን ታሪካችን ነው። ዛሬም ያው የባሰ እና የከፋ የገለማ ዘመን ቢያጋጥመንም የዚህች መከረኛ አገር ልጆች ይባስ ብለው በዘር ተጠርንፈው እየዳከሩ መሆኑን ስናይ ከከባድ ሐዘን ጋር ነው።

የዚህ የዘረኛው የትግሬ ስርአት ካበቃለት ሰነባብቷል። እንዴውም መሪወቹ በአገራችን ታሪክ ተሰምቶም ሆነ ታይቶ በማይታወቅ ንቅዘት ተዘፍቀው እብሪት እስከ አንገታቸው ወጣጥሯቸው የአሉበትን ሁኔታ ለመገንዘብ አቅምና ችሎታ የላቸውም። ሆኖም ከመጨረሻዋ ጠርዝ ላይ እንዳሉ ግን የሚካድ አይደለም። አሳዛኙ ግን በተቃዋሚው ጎራ ዛሬም በባሌና ቦሌ የስልት ልዩነት ከ 40 አመታት የሰናይ ልኬ ከንቱ ምኞትም በኋላ አልተስተካከለም። የያኔው ተማሪና አስተማሪ፣ ሰራተኛ እና አርበኛ አንድ ሀገር፣ አንድ ሰንደቃላማ አንድ ሕዝብ ብሎ የዘመረና የታገለ። በአመነበትም በቦሌም ሆነ በባሌ ገብቶ ሕይወቱን ያሳለፈ ትውልድ ነበር። ይህንና ያነን የሚያገናኛቸው ባህርይ ግን የዘንድሮው መሪ አልባነት ሳይሆን። የያኔው መሪው ቀድሞ ከታጋዩ በፊት መስዋት መሆን ነበር።

ዛሬ ከምንግዜውም በላይ አታጋይ መሪ የሚፈለግበት ወቅት ነው። መሪ ሁሉም ነገር ነው። መሪ ስንል እርስ በእርስ የሚያናክስ። በቂም ተለውሶ የሚርመጠመጥ ሳይሆን ይህን እየተነሳሳ ያለን የዘር ጉግ ማንጉግ ለአገራዊ ድል እንዲሰለፍ ማድረግ ነው። ድርጅትና መሪ ለዚህ ጊዜ ካልሆኑ መቸ ነው የምንፈልጋቸው? በሰላም ጊዜ ወይንም ነጻነትና እኩልነት ከተከበረ። የአገር አንድነት የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ከታወቀ በኋላ ሌላ ምእራፍ፣ ሌላ ትውልድ፣ ሌላ የፖለቲካ ባህል ነው የሚተካው። የዛሬወቹ ለዛሬ እንጅ ለሌለ ነገ መሆን አይችሉምና።

የድርጅቶች በባሌና በቦሌ እሰጥ አገባውን ትተው ሕዝቡን ለማደራጀት በአንድ ይነሱ። ትብብር ዛሬ ነው። ሁሉም ከመሸገበት ጓዳ መውጣት ያለበት ዛሬ ነው። ይህ እድል ካመለጠ። ወይንም የተጀመረው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ወያኔ በቆፈረለት የዘረኝነት ቦይ ከፈሰሰ ድል ከሰማይ የራቀ እንደሚሆን መጠራጠር የለብንም። የኦሮሞ ተማሪወች፤ ወይንም የአማራ ብለን በአፍ ሞልተን መናገሩ በእራሱ ከባድ ችግር እንዳለብን እና ስልጣን ከወያኔ ብታመልጥ እንኳን ለሕዝብ እንደማትሆን ማወቅ

ይኖርብናል። የዚህ ውጤት ደግሞ በጓዳ ሂድ በበር ያው የወያኔ ድል ሆኖ የሚቋጭ ነው። በእርግጥም የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ሕዝብን ጎጅ ነው፤ ወያኔን ጠቃሚ ነው ካልን ትግሉን አገራዊ ቅርጽ እንዲይዝ ማድረግ በኦሮሞ ታጋዮችም ሆነ በሌሎች ኢትዮጵያውያን መካከል ወያኔ የዘረጋውን ወጥመድ መስበር። ለአንድ አላማ በአንድ እንዲነሳሳ ማድረግ ግዴታም ታሪካዊ ሀላፊነትም ነው። እንደ ቦዝኒያ ሄርሶ ጎቬና የህዝብን ጥያቄ ለልዩ አጀንዳ ላላቸው መሪወች አስረክበን የእርስ በእርስ መጠፋፋትን ድልድይ አንዘረጋም።
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!! ሕዝባዊው ትግል ግቡን ይመታል!!!
http://www.ethiopanorama.com